# መለመን ...
# ከሁሉም ወገን፣ ነገድ ፣ ሕዝብ እና ቋንቋ

**ASKing ... for those from every Nation, Tribe, People & Language in Urdu**

መንፈሱና ሙሽራይቱም። ና ይላሉ። የሚሰማም። ና ይበል።
የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።
የዮሐንስ ራእይ 22:17

< <አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ በዙፋኑና በበጉ ፊት የሚቆሙበትን ቀን> > በጉጉት እንጠብቃለን። ራዕይ. 7፡9
በዚያን ቀን ልመናችን ይቆማል ነገር ግን እስከዚያ ድረስ ለዚያ ታላቅ ቀን መምጣት ፀሎታችን ማዘጋ ት ይችላል ፤ አለበትም!
እበዚህ < <ሕዝብ፣ ነገድ፣ቋንቋ እና ወገን> > የሚሉ አራት ቃላቶች በራዕይ መጽሐፍ አምስት ጊዜ ተጠቅሰዋል ነገር ግን በአንድ ዓይነት ቅደም-ተከተል አይደለም፤ ይህ የሚያሳየን አራቱም በእግዚአብሔር ዓይን ፊት እኩል ዋጋ እንዳላቸው ነው። ራዕይ 5፡9፣ 7፡9፣ 11፡9፣ 13፡7፣ 14፡6

## ለ ሀገሬት መለመን

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገሬት 600 ማጠቀሻዎች መኖራቸው እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን የታሰበበት ንድፍ እና የመዋ ት ዓላማን ያሳያል። በዚህ አውድ ሀገራትን መልክዓ-ምድራዊ ድንበሮች ያለቸው እና በመንግስት የሚተዳደር መሬት ብለን ልንተረጉመው እንችላለን።

ለራሳችሁ ሀገር ለምኑ. እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። 1ጢሞቴዎስ2፡1-2

ጠንካራ ደቀ-መዝሙር ያለው ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ገሬት እንዲመሰረት እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።ጸልዩ. የማቴዎስ ወንጌል 28:19-20

ለ ሀገራት በሙሉ ለመጸለይ የሚያስችለውን እቅድ ተከተሉ. www.operationworld.org የሚለው ድህረ-ገፅ ብዙ መርጃ መሳሪያዎች አሉት

## ለሕዝብ መለመን

ጌታ ለያዕቆብ < <በአንተና በዘርህ አህዛብ ሁሉ ይባረካሉ።> > ብሎታል። የእርሱ ዘሮች ደግሞ የአይሁድ ሕዝቦች ናቸው። የሕዝብ አቦዳደንን ስንወስን በዘር ላይ የተመሰረተ አቦዳደንን ልንጠቀም ይችላል፤ እንዳንዴ ይህ ከአህጉራዊ አቦዳደን ጋር ሊጋጭ ይችላል። ይህ ለፀሎት ሰዎችን ለመለየት ይረዳል፤ እግዚአብሔርን ልዩ ማንነቶቻቸው እና ባህሎቻቸው የእግዚአብሔርን ክብር በሙላት እንዲገልጥ መለመን ያስፈልጋል።

የሁሉም ሰዎች ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን ይህ መገለጠ ወደ ሰዎች ሁሉ እንዲደርስ እየጸለያችሁ ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።አምልኩት። መዝሙረ ዳዊት 24:1

በሕዝቦች መካከል የዘረኝነት መከፋፈል በተለይ በዓለም ሁሉ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰበር ጸልዩ። የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። የማቴ.5:9

የመከሩን ጌታ ወንጌል ወደ እያንዳንዱ ሕዝብ በኃይል እንዲሄድ ለምኑት። ደግሞም፦ እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ፥ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት ይላል። ወደ ሮሜ .15:11

## ለቋንቋዎቹ መለመን

ዛሬ በዓለም የሚነገሩ ቋንቋዎች ቁጥር በትንሹ 6800 ደርሷል። ምንም ዓይነት መጽሐፍ የሌላቸው ነገር ግን ለመ  መር የሚያስችል የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ቁጥር ከ2000 ይበልጣል፤ ይህም 300 ሚሊዮን ሕዝብ ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል።

እያንዳንዱ ሰው በራሱ ቋንቋ ወንጌልን መስማት ይችል ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እያንዳንዱ ቋንቋ እንዲተረጎም ጸልዩ። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?ወደ ሮሜ.10:14 እግዚአብሔር የwww.wycliffe. www.pioneerbible.org www.lbt.org ሥራን በአቅርቦት እንዲባርክ እና መከናወን እንዲሰጣቸው ጸልዩ። የአምላካችን የእግዚአብሔር ብርሃን በላያችን ይሁን፤ የእጆቻችንንም ሥራ በላያችን አቅና። መዝሙረ ዳዊት 90:17

እግዚአብሔር የባቢሎን ግንብ ከተሰራ በኋላ ያስተላለፈውን ፍርድ እንዲቀለብስ ጸልዩ:: ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ፥ እግዚአብሔር በዚያ የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና ከዚያም እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ እነርሱን በትኖአቸዋል። ኦሪት ዘፍ.11:9

## ለነገዶቹ መለመን

በእስራኤል  ገር 12 ነገዶች ነበሩ። ብዙ የዓለማችን  ገራት ውስጣዊ የነገድ ሥርዓት አላቸው። አብዛኛውን ጊዜ በቋንቋ፣ በአኗኗር ዘይቤ እና በመልክዓ ምድር ይለያሉ። በአንድ  ገር ወንጌል ያልደራሳቸው ነገዶች መገኘታቸው የተለመደ ነው።

ወንጌል ያልደረሳቸው ሕዝቦች በሚጸልዩ ቡድን ውስጥ ተሳተፋ።በ7000 የሚገመቱ ሰዎች ወንጌል ያልደረሳቸው ሕዝቦች ናቸው። ይህ ማለት 41% ወንጌል አልደረሳቸውም። ያ ማለት 2.84 ሰዎች ናቸው። www.joshuaproject.net ተቀላቅላችሁ በየቀኑ ስለምትፀልዩላቸው የተለያዩ ወንጌል ያልደረሳቸው ሕዝቦች መረጃ ማግኘት ትችላላችሁ።

በቴክኖሎጂ ስጦታ እና በኢንተርኔት በኩል በጣም ፈጣን እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ከምድር ጫፍ እስከ ጫፍ እንዲገሰግስ ጸልዩ። ችግረኞች ይበላሉ፥ ይጠግቡማል እግዚአብሔርንም የሚሹት ያመሰግኑታል ልባቸውም ለዘላለም ሕያው ይሆናል። የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስቡ፥ ወደ እግዚአብሔርም ይመለሱ የአሕዛብ ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ። መዝሙረ ዳዊት 22:26-27

ክብሩን ለአሕዛብ፥ ተአምራቱንም ለወገኖች ሁሉ ንገሩ።
1ዜና . 16:24
አስክ ኔትወርክ ለእያንዳንዱ ወገን፣ ነገድ፣ ሕዝብ እና ቋንቋ ስለኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት እስኪያውቁ ድረስ በመጸለይ ፍፃሜውን ማሳካት ይችላል። አሜን።